# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ ስፖርት ፖሊሲ

## መግብያ

- ስፖርት፡- ማንኛውም ግለሰብ ዕድሜና ፆታ ሳይገድበው **ጤንነቱን ለመጠበቅና ለመዝናናት፤አካሉን ለመገንባትና አእምሮውን ለማበልፀግ ፤አቅሙንና ችሎታውን ለመመዘን** በግሉ/በጋራ በተደራጀና በልተደራጀ መልክ በማንኛውም ጊዜና ቦታ የሚያከናውነውን የተለያየ የአካል እንቅስቃሴ ያጠቃልላል፡፡
- የስፖርት እንቅስቃሴ መሰረቱ የሰው ልጅ ብሎም ሕ/ሰቡ ነው፡፡ በስፖርት እንቅስቃሴ **መሳተፍ ጤናማ የአካልና አእምሮ ያጎናፅፋል፤ በማህበራዊ ግንኙነትን በኩል መተዋወቅን፤ መቀራረብን፤ አብሮ መኖር፤ መስራትንና ቤተሰባዊ ፍቅርን ያጠናክራል፡፡** ይህ ግንኙነትን እየዳበረ በመሄድ ብሄርብሄረሰቦችንና ሕዝቦችን በማቀራረብ ግንኙነታቸው እንዲዳብርና አንድነታቸው እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡

# የቀጠለ…

- ሰፊ መሰረት ካለው የስፖርት እንቅስቃሴ የተገነባ አካልና አእምሮ ፡ - በኢኮኖሚው ዘርፍ የተሻለ ምርት ያመርታል፤ ጤይንነቱ የተጠበቀ ዜጋ ይፈጠራል( ለህክምናና ለመድሓኒት የሚወጣ ወጪ ይቀንሳል) ፤ ምርጥ ስፖርተኞችን ይገኛሉ ( በአለም አቀፍ ውድድሮች በመሳተፍ ሀገራችን እንድትታወቅና ከሌሎች አገሮች ጋር የሚኖራት ግንኙነት እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡
- የአገራችን የስፖርት ሁኔታ ሲታይ የነበረው ትልቁ ችግር የአደረጃጀት( ህዝባዊ መሰረት ያልነበረው) ፤ አመራርና የአመለካከትና ( ተተኪ ስፖርቶኞችን ያለማፍራት ፤ የት/ቤቶች ስፖርት መዳከም ፤የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች እጦት፤ ትጥቅና መሳርያዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖርና የሰለጠነ በለሙያ እጥረት) የትኩረት አቅጣጫ( ሕ/ሰቡ በሰፊው በስፖርት በማሳተፍ ምርጥ ስፖርቶኞችን ያለማፍራት) ናቸው ፡፡

# 1. የፖሊሲው ዓላማ

- የስፖርት እንቅስቃሴ ማከናወን የዜጎች መሰረታዊ መብት መሆኑን ተግባራዊ ለማድረግ ሕ/ሰቡ በባህላዊ ስፖርቶችና በስፖርት ለሁሉምና መዝናኛ አቅሙ በፈቀደ መጠን እንደየፍላጎቱ የሚያደርጎውን ተሳትፎ ማጎልበት፡-
  - ከአጠቃላይ የሕ/ሰቡ የስፖርት እንቅስቃሴ በመነሳት በተለይ የወጣቱን ትውልድ ግንዛቤና ተሳትፎ በማጠናከር የላቀ ችሎታ ያላቸውን ምርጥ ስፖርቶኞችን በማፍራት በአለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ፡-

# 2.የፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫ

- የስፖርት አጠቃላይ እንቅስቃሴ አደረጃጀትና አመራር ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ይደረጋል
- ህ/ሰቡ በሚኖርበት ፤በሚማርበትና በሚሰራበት አከባቢ በስፖርት እንቅስቃሴ ተሳታፊ የሚሆንበት ሁኔታ ይመቻቻል
- አርሶ አደሩ በባህል ስፖርቶች በስፋት መሳተፍ የሚችልበት ሁኔታ ይመቻቻል፤

2. የፖሊሲው የትኩረት አቅጣጫ

- ሴቶች በስፖርት እንቅስቃሴ ቀጥተኛ ተሳታፊና በእኩል ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፤
- ስፖርት ከመንግስት በጀትና ድጎማ ደረጃ በደረጃ የሚላቀቅበትና ራሱን የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል

# የቀጠለ…

- መንግስትና ሕ/ሰቡ ሕዝቡ በሚኖርበት ፣በሚማርበትና በሚሰራበት አከባቢ ለስፖርት እንቅስቃሴ ማዘውተርያና ለመዝናኛ የሚሆን የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራ እንዲጠበቅና እንዲገነባ ይደረጋል
- የስፖርት እንቅስቃሴ ማዘውተርያነት የሚያገለግሉ የስፖርት ትጥቆችና መሳርያዎች በአገር ውስጥ የሚመረቱበትን ሁኔታ ይመቻቻል
  - የአገሪቱን የተማረ የሰው ኃይል ችግር ለመቅረፍ የስፖርት ባለሙያዎች በብዛትና በጥራት የሚፈሩበት ሁኔታ ይመቻቻል።

# 3. የፖሊሲው የአፈፃፀም ስልቶች

- ሕ/ሰቡን እንደየፍላጎትንና እንደየችሎታው በሚኖርበት ፤በሚማርበትና በሚሰራበት አከባቢ በማደራጀት በግሉና በጋራ በስፖርት እንቅስቃሴ እንዲሳተፍ ማድረግ፡፡

# 3.1. በመኖርያ አከባቢ

- ሕ/ሰቡ እንደየፍላጎቱ በስፖርት ለሁሉምና መዝናኛ ፕሮግራም እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- አርሶ አደሩ በባህል ስፖርቶች እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- ቡድኖችንና ክለቦችን በማቋቋም ሕ/ሰቡ በውድድር ስፖርቶች እንዲሳተፍ ማድረግ፤
- በቀበሌ፤ በወረዳ፤ በዞንና በክልል የሚገኘው ሕ/ሰብ በስፖርት እንቅስቃሴ ለመሳተፍ እንዲችል የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎችና መዝናኛዎች በገጠሩ እንደህዝቡ አሰፈሰፈርና በከተማ በማስተር ፕላን እንዲያዙና እንዲገነቡ ማድረግ
- ሕ/ሰቡ በስፖርት ማዘውተርያ ግንባታ እንዲሳተፍ በተለያየ መንገድ ማበረታታት

☒

## 3.2. በትምህርት ተቋማት

- ከትምህርት ተቋማት ጋር የአሰራር ቅንጅት በመፍጠር ከመዋዕለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሚዘጋጀው ስርዓተ ትምህርት ውስጥ የባህል ስፖርትን ጨምሮ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በቂ ክፍለ ጊዜ በመመደብ ተማሪዎች በስፖርት እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- መዋዕለ ሕፃናትና ት/ቤቶች በሚገነቡበት ጊዜ የስ/ማ/ስፍራዎች በመሪ ፕላናቸው ውስጥ እንዲካተቱና እንዲገነቡ እንዲሁም የስፖርት ትጥቅና መሳርያዎች እንዲሟሉ ማድረግ፤
- በትምህርት ተቋማት የስፖርት ክበባትን በማቋቋም ህፃናትና ወጣቶች እንደየፍላጎታቸውና ዝንባሌያቸው በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

# የቀጠለ...

- የውድድር መርሐ ግብር በመዘርጋት ተማሪዎች በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች እስከ አገር አቀፍ ደረጃና ከዚያም አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዩንቨርስያድ ውድድሮች እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- ከስፖርት ክለቦችና ፌዴሬሽኖች ጋር የአሰራር ቅንጅት በመፍጠር በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች በመመልመል ልዩ ስለጠና የሚያገኙበትንና በተለያዩ ውድድሮች የሚሳተፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- በት/ቤቶች የሚገኙ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ከአካል ጉዳታቸው ጋር ተስማሚ በሆነ የስፖርት እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- በትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚገኙ መምህራንና ሰራተኞች እንደየፍላጎታቸው በተለያዩ የስፖርት እንቅስቃሴዎች የሚሳተፉበትን ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

# 3.3. በመስርያ ቤቶች

- ከመንግስትና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የአሰራር ቅንጅት በመፍጠር በሚሰሩበት አከባቢ በተለያየ የስፖርት እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- በተለያዩ መስርያ ቤቶችና ድርጅቶች የስ/ማ/ስፍራዎች እንዲከለሉና እንዲገነቡ ማድረግ

## 3.4. በሰራተኛ ማህበራት

- ከሰራተኛ ማህበራት ጋር የአሰራር ቅንጅት በመፍጠር ሰራተኛው በሚሰሩበት ድርጅት በተለያዩ የስፖርት እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- ሰራተኛው የስፖርት ክበብ በማቋቋም በተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች እንዲሳተፉ ማድረግ።

# 3.5. በአገር መከላከያና በፖሊስ ሰራዊት

- በአገር መከላከያና በፖሊስ ሰራዊት ጋር የአሰራር ቅንጅት በመፍጠር የሰራዊቱ አባላት በተለያዩ የስፖርት እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- የመከላከያና የፖሊስ ተቋማት በሚገነቡበት ጊዜ የስ/ማ/ስፍራዎች በመሪ ፕላን እንዲካተቱና እንዲገነቡ ማድረግ፤
- የመከላከያና የፖሊስ ልዩ ልዩ ክፍሎች
- ክለብ በማቋቋም በተለያዩ ውድድሮች እንዲሳተፉ ማድረግ፡፡

# 3.6. በጤናና በስፖርት ሕክምና ተቋማት

- ከተለያዩ የጤና ተቋማት ጋር የአሰራር ቅንጅት በመፍጠር የስፖርት እንቅስቃሴ ጠቀሜታ በተቋማቱ የሚተላለፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፤
- የስፖርት እንቅስቃሴ ከዘመኑ ትምህርት ፤ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር በተጣጣመ መልኩ ማደግ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፤
- የስፖርት ሕክምና የማገገሚያ ስፍራዎች እንዲኖሩ ማድረግ፤
- ሕ/ሰቡ የስፖርትን ፅንስ ኃሳብና ጥቅም ተገንዝቦ በእንቅስቃሴው ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የማስተማርና የቅስቀሳ ተግባር ማከናወን፤
- ሴቶች በሚኖርበት ፤በሚማርበትና በሚሰራበት አከባቢ ለስፖርት እንቅስቃሴ ቀጥተኛ ተሳታፊና በእኩል ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- አካል ጉዳተኞችን በሚኖርበት ፤በሚማርበትና በሚሰራበት አከባቢ ለስፖርት እንቅስቃሴ ቀጥተኛ ተሳታፊና በእኩል ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

# 4. የስፖርት አደረጃጀትን አመራርን ግንኙነትና ፋይናንስን በተመለከተ

- የሀገሪቷን ስፖርት በበላይነት የመምራት ስልጣን የሕዝባዊ አካሉ /ክለቦች፤ ፌዴሬሽኖች፤ ኦሎምፒክ ኮሚቴና የስፖርት ምክር ቤቶች / ሆኖ በየደረጃው ያሉ መንግስታዊ አካላት / የስፖርት ኮሚሽኖች/ ሕዝባዊ አካሉን የመደገፍና የማገዝ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ፤
- ከተለያዩ መንግስታትና የስፖርት ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር፤
- ለስፖርት የገቢ ምንጭ እንዲፈጠር በተለያየ መንገድ መደገፍ፤
- በለሃብቶች በስፖርት ኢንቨስት እንዲያደርጉ በተለያየ መንገድ መደገፍ

## 5. የስፖርት አንስቲትዩትና ስልጠናን በተመለከተ

- የአገሪቱን የባለሙያ እጥረት ለመቅረፍና የአቅም ግንባታ ተግባራትን ለማከናወን እንዲሁም የጥናትና ምርምር ተግባራትን ለመፈፀም ፤ የስፖርት  አንስቲትዩት የሚቋቋምበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- የተለያዩ የስፖርት በለሙያዎችን በአገር ውስጥና በውጭ አገር ማፍራት
- የስፖርት ማበልፀግያ ማዕከላት በየደረጃው ማቋቋም፡፡

# 6. ባህላዊ ስፖርቶችን በተመለከተ

- የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች ባህላዊ ስፖርቶች እንዲመዘገቡና በጥናት ተለይተው ህግና ደንብ ወጥቶላቸው በአርሶ አደሩ እንዲዘወተሩ ማድረግ፤
- ብሄር ብሄረሰቦችን ማዕከል ያደረገ አገር አቀፍ ውድድር ማዘጋጀት፤
- የባህል ስፖርቶች ፌስቲቫሎች ማዘጋጀት፡፡

## 7. የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎችን በተመለከተ

- የፈጠራ ስራዎችን በማዳበር ከሕ/ሰቡ አቅም የሚመረቱበትን ሁኔታ ማበረታታት።

# 8. የፖሊሲው አስፈፃሚ አካላት

- በየእርከኑ የሚቋቋሙ መንግስታዊ አካላት
- በየደረጃው የሚዋቀሩ የስፖርት ምክር ቤቶች
- በየደረጃው የሚቋቋሙ የስፖርት ፌዴሬሽኖች

- በተለያዩ የስራ ዘርፎች የሚገኙ መንግስታዊና ህዝባዊ ድርጅቶች፡፡